# እንዲያው ለነገሩ…?

(ከአያልነሽ)

ውሃ ሲውስድ እያሳሳቀ ነው ይላሉ የአገሬ ሰዎች። ይህንን ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለምና ምክንያቴን ወደ ኋላ ላይ እደረድራለሁ። ምክንያቴን ስደርድር ግን አንባቢዎችን በቅድሚያ የምጠይቃችውና በአዕምሯቸው ውስጥ እንዲያብሰልስሏችው አንዳንድ ጥያቄ መስል ሃሰቦቸን በመስንዘርም ጭምር ነው። መጠይቃዊ ሃሳቦቼ አንባቢዎቼን የሚያደክሙብኝ/የሚያሰለቹብኝ ሆነው ከሆነ ግን ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

1/ እኔ ኢትዮጵያን እወዳለሁና እንደኔ እናት አገራችንን ኢትዮጵያን የሚወድ/የምትወድ/የሚወዱ/የምትወዱ ከሆነ ሁላችንም ኢትዮጵያን እንወዳለን የምንል ሁሉ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነን ሁሉ ልንጠላ እንገደዳለን ማለት ነው። እስቲ ማነው እናቱን ሲጠሉበት/ሲጠሉባት በእናቱ/ቷ ላይ የጥላቻ እንቶ ፈንቶና የስድብ መርዝ ሲያወርድበትና/ሲያወርድባት ለማዳመጥ ትዕግስት የሚኖረው/የሚኖራት/የሚኖራቸው? ኢትዮጵያ ለእኔ እንደዚያ ናት። ወገኖቼ! ለእናንተስ?

2/ የኔ ጠላት ህዝቤንና ህዝባችንን የሚንቅ፣ የሚያዋርድ፣ በእኔና በኢትዮጵያዊነቴ ላይ የሚሳለቅ፣ ታሪኬን (እንደ ወፍ ዘራሽ ነገር) ፈሶ እንደተለቀመ ጥሬ፣ ወድቆ እንደተገኘ ጉዳይ አድርጎ የሚመለከትብኝን ነጭም ሆነ ጥቁር ጠላቴ እላለሁና ወገኖቼ! እናንተስ?

3/ ከየትም አቅጣጫ ይምጣ ከየትም፣ ማንም ያምጣው ማን፥ ባህሉን፣ ወጉን፣ አገሩን፣ ህዝቡን እንዲሁም ማንነቷንና/ማንነቱን እንዳከብርለት እንደሚጠይቀኝ ሁሉ ባንፃሩ እኔም ባህሌን፣ወጌን፣አገሬን፣ ህዝቤንና ማንነቴን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባብኝን ሁሉ ጠላቴ ነው እላለሁና ወገኖቼ! እናንተስ?

4/ እኔ ጠላት የምለው አገሬ ኢትዮጵያን ለማጥፋት፣ ፀሐይ በወጣችና በገባች ቁጥር እንዲሁም ሌት ተቀን ይሁነኝ ብሎ ሲባዝን፣ ሳይተኛ ለሚያድር፥ ነጭ ሆነ ጥቁር ለማንኛውም ሰው ወይም ህይል፤ የአገሬ ነገር አይሆንልኝምና እኔም እንደነእርሱ አልተኛም ብላችሁ ክፉ ሰው ትሉኝ ይሆን? ወገኖቼ! እናንተስ?

5/ እኔ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ነኝና ተጠራጣሪ ነኝ። እባብ ያየ ….ተብሏልና እኔ አገሬን በክፉ ዓይኑ የሚያይብኝን ሁሉ እጠራጠራለሁኝ እናንተስ? ወግኖቼ መጠራጠሬን ትጠሉብኝ ይሆን?

6/ ለእኔ ለኢትዮጵያዊነቴ መግለጫዎች የሆኑ ማንኛቸውም ነገሮች (መጥፎም ሆነ ጥሩ) ጥሩነቱን ሆነ መጥፎነቱን የሚነግረኝ ኢትዮጵያዊው/ዊቷ

ወገኔ እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም ባይ ነኝና ወገኖቼ! እናንተስ? ወዘተ.ወዘተ ወዘተ......።

ታዲያሳ! ፅሁፌን ስጀምር «ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ» ነው ብያለሁ። ለምን እንደተጠቀምኩበት ምክንያቴን እደረድራለሁ ስላልኩ የተጠቀምኩበት ምክንያት እነሆ!

ሚለኒየም፥ ቃሉን የሰማሁት ፈረንጆች 1999ዓ.ም-ን አገባደው ወደ ሁለት ሽህ ዓ.ም ሲገቡ ያንን ከ1999ዓ.ም ወደ 2000ዓ.ም የተሸጋገሩበትን ወቅት (መሸጋገሪያውን) ሚለኒየም ብለው ሲጠሩት ነው። ያውም አጠራሩ እንድየአገሩ የተለያየ እንደነበር ይታወቃል። ይህ ጊዜ በተለይም በአውሮፓና አሜሪካ በተለየ ድምቀት እንደተከበረና ሁሉም ማለት ይቻላል ሚለኒየምን (ያችን ቀን) የተለየች ቀን አድርገው እንደተመለከቱት ታዝቢያለሁ። ለእኔ ግን ያች ቀን ምኔም አልነበረችምና፣ የነርሱ ደስታ ግን የኔም ሆና ማለፏን አስታውሳለሁ። ለእኔ በነርሱ አገር እየኖርኩ የነርሱን ባህል ማክበር ይገባኛልና አብሬያቸው የደስታቸው ተካፋይ ነበርኩ። እነርሱ ሚለኒየም ብለው ሲጠሩት(እነርሱ በ2000 ዓመት ያገኙአቸው ፀጋዎች ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ) የሚለኒየማቸው ትርጉም ቦታውና አገሩ ነውና በርግጥም በአግባቡ ተጠቅመውበታል። ታዲያ ይህንን ቃል በፈረንጆች አገር ከሰማሁት በኋላ ዛሬ ደግሞ በእኛይቱ አገር ኢትዮጵያ ውስጥ "ሚለኒየም"ን ለማከበር ሽር ጉድ እየተባለ ነው። ለመሆኑ "ሚለኒየም" ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ህዝብ ምኑ ነው? ይህ ሁሉ ወጭ እየተደረገ ከኢትዮጵያችን አልፎ በምድረ አውሮፓና አሜሪካ ድረስ በወያኔና አጋፋሪዎቹ ጥሩንባ የሚነፋለት ሚለኒየም፣ የማን ነው? እኛስ ወያኔ ከባዕዳኖች የወሰደውን ስምና ለእርሱ ኪስ መሙያ የሚጨኸበትን የራሱን በዓል ሚለኒየም እያልን ስናስተጋባለት፣ አውቀነውም ሆነ ሳናውቅ በራሳችን የቆየ ባህል ላይ እየዘመትን መሆኑን አስተውለናል? ፀረ ኢትዮጵያ የሆነውንና ባህላችንን ለማጥፋት ያልተኛውን የወያኔን አገዛዝ፣ እነ መለስን ምን ያህል እየረዳናቸው እንደሆነ ተገንዝበነዋል? ቃሉንስ ከነርሱ ተቀባብለን ወስደን ምን ያህል እየተለማመድነው መሆኑን ልብ ብለናል? ለዚህም ነው ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው ያልኩት። በነገራችን ላይ የወያኔ "ሚለኒየም" በሶስት መሰረታዊ ነገሮች ላይ ያነጣጠረ ነው።

1ኛ/ ከግንቦቱ ምርጫ ጋር በተያያዘ በምርጫ መሸነፉንና ከዚያም ጋር ተያይዞ በተከታታይ የወሰደውን ፋሽስታዊ እርምጃና እመቃ ለማረሳሳት፣

2ኛ/ ከምርጫው በኋላ የተሸነፈና ህጋዊነትም ስለሌለው፣ ይህንን ህጋዊ ያልሆነ አገዛዙን ለማቆየት ከሚጠቀምበት ስልት እንደአንዱ በመሆኑ፣

(በየጊዜው አዳዲስ ስልት እየወለደልንና በመቀያየር እየሰራልን መሆኑን ልብ እያልነው ነው? ። የሶማሊያ የጦርነት ጥሪም የዚሁ ተምሳሌ ነው።)
3ኛ/ ህወሃት/ወያኔ ከመጀመሪያው ጀምሮ ጸረ-ኢትዮጵያ የሆነ ቡድን በመሆኑ ባህላችንን፣ ኢትዮጵያንም ለማጥፋት የሚያረገው እንቅስቃሴ መሆኑ፣ በግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው።
በጉልበት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በዚህ በኩል ብዙ የደከመ/ያልቦዘነ ስለሆነ ኢትዮጵያዊ የሆናችሁ ወገኖቼ ሁሉ ይህንን የወያኔን "ሚለኒየም" ከስሙ ጀምሮ መቃወም አለብን እላላሁ። መጀመሪያውኑም ስሙ ራሱ የኛ አይደለም። እኛ የምናከብረው በዓል ከሆነ ደግሞ ሲወርድ ሲዋረድ የቆየ ባህል ስላለን ያንን መሰረት ያደረገና በራሳችን መንገድ  እንድናከብረው በትህትና እጠይቃለሁ።
ወገኖቼ! ከላይ መጀመሪያ ላይ ከ1-6 የዘረዘርኳቸውን መጠይቃዊ ሃስቦች እየአብሰለሰላችሁ ከሆነ እኔ የወያኔን "ሚለኒየም" ከስሙ ጀምሮ ስቃወም እንዲያው በደፈናው «ጠብ ያለሽ በዳቦ» በሚባለው ዓይነት ሳይሆን የመለስ ወያኔያዊ አገዛዝ ኢትዮጵያን የማይወክል፣ ፀረ-ኢትዮጵያና የህዝባችን ጠላት በመሆኑ ነው። ይህንን በማለቴ የማሳዝነውና የማስከፋው ሰው ካለ ይቅርታ እጠይቃለሁ። እኔ ማንንም ለማሳዘን ወይም ለማስከፋት አስቤ አይደለም። ኢትዮጵያን እወዳለሁ ብያለሁና አገሬ ኢትዮጵያን የሚጠሉትንና የሚያጣጥሏትን ካስከፋቸው በጣም አዝናለሁ። ጥፋቱ ግን የኔ አይደለም። እኔ መቆሚያየ ኢትዮጵያ ናትና። ኢትዮጵያውያን ወገኖቼና እኔ ደግሞ፤ የራሳችን የሆነ ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ ያለን ስለሆነ፣ ወያኔ የማያውቃትን ኢትዮጵያንና አላውቀውም የሚለውን ባህላችንን እንዲያውቀው ማድረግ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ፍላፊነትና ግዴታ ነው እላለሁ።
ለነገሩማ በሀገራችን በኢትዮጵያ የምንኮራ ዜጎቿ ሁሉ፣ በምንኖርበትስ የፈረንጅ አገር የራሳችን የሆኑ ባህሎቻችንን ከማስተዋወቅ መች ቦዝነን እናውቃለንና!